# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

## በኢትዮጵያ በሬዲዮ ስርጭቶችና ድረ-ገፆች ላይ
## የተጣለው እቀባ አሁንም እንደቀጠለ ነው

በኢትዮጵያ በሥልጣን ላይ ተቆናጦ ያለው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ የተቃዋሚ የሬዲዮ ስርጭቶችና ድረ ገጾች አልተገደቡም ሲል የተሳሳተ አስተያየት ማስተጋባቱ ተደምጧል። ይህንን አይን አውጣ ቅጥፈቱንም ለማጠናከር ይረዳው ዘንድ በቅርቡ አንድ የአገዛዙ ባለሥልጣን የሆነ በግልፅ እንደተናገረው ቀደም ሲል ተገድቦ የነበረ የተቃዋሚ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ስርጭት ያለምንም ተአቅቦ ይሰማል ሲል በምሳሌነት ጠቁሟል።

ምንም እንኳ ይህ ባለሥልጣን በምሳሌነት የጠቆመው የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ስርጭት የቴሌቪዥን መቀበያ መሳሪያ ባላቸው ዜጎች ለመመልከትና ለመደመጥ የሚቻል ቢሆንም በሌሎች የሬዲዮ ሥርጭቶችና ድረ-ገጾቻቸው ላይ የተጣለባቸው እገዳ ተነስቷል የሚል ግምትና አስተያየት ጨርሶውኑ ከዕውነቱ የራቀ ነው። አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነዚህ ተቋማት ዜናን በነፃ የማግኘትና ድረ-ገጾቻቸውን የመመልከት በሩ ተከርችሞበታል።

ለምሳሌ እንደ ደብተራው፣ አሲምባ፣ ኢትዮላየን፣ የኢሕአፓ ድረገጽ፣ በሀገራችን ለሰብአዊ መብት መከበር የሚንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የመሰሉና ሌሎችም ድረ-ገፆች በራሱ በአገዛዙ ቃል ለፀጥታና ለመረጋጋት በሚል ሰበብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መገደባቸው እንደቀጠለ ነው። ኢሕአፓ በበራሪ መግለጫዎቹ በተደጋጋሚ እንደገለፀው ፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዩ ስርጭት ቢያንስ ላለፉት አምስት አመታት በባዕዳን የቴክኒክ እርዳታ በመታገዝ እንዳይደመጥ መደረጉ አሁንም አልተገታም። በዚህም የተነሳ ኃሳብን በነፃ የመግለፅና የፕሬስ ነፃነት የመከበር መብቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር የሕግ እውቅና ያገኙትን ተቀብያለሁ በማለት በራሱ ሕገ አገዛዝ ያካተታቸውንና ራሱም የደነገጋቸውን  ሕጎች ሳይቀር ተጻርሮ ያለ አገዛዝ ነው። ኃሳብን ያለ ቅድመ ሳንሱር የማንሸራሸር መብት በኢትዮጵያ እየተከበረ ነው ተብሎ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም የወያኔ አገዛዝ በአዙሪት ይህንኑ መብት በተግባር ተቃርኖ ይገኛል። ይህ የተቃውሞ ተግባሩ የሚገልፀው ደግሞ፡-

1. አብዛኛዎቹን የሕትመት ተቋማትን በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በማስገባት፤
2. በአገዛዙ ላይ የሰላ የተቃውሞ ትችት የሚያቀርቡ መፅሃፎችን ለማተም ጥረት የሚያደርጉ አሳታሚዎችን በማስፈራራት፤
3. የተቃውሞ ትችት ያዘሉ መፅሃፍቶች ለመታተም የበቁም ቢሆኑ ለሽያጭ ከተደረደሩ ሱቆች የራሱን የፀጥታ አባላት እየላከ ሻጮቹን በማስፈራራትና መፅሃፍቱን እንዳይሸጡ፤

በማድረግ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ በአገዛዙ ላይ ከፍተኛ ነቀፌታን ያዘሉ መፅሃፍት ወደ አደባባይ ብቅ ለማለት ቢችሉም በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ ደራሲያንን፤ ገጣሚዎችንና ጋዜጠኞችን ከአገዛዙ የቅጣት መዝገብ ውስጥ አካትቶ በአይነ ቁራኛ እንደሚጠብቃቸውም ይታወቃል። ተጨባጭ ሁኔታውም የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው።

ለዚህም ነው በራሱ ኃላፊነት የሚሰራጩ የሬዲዮ ፕሮግራሞችና ድረ-ገፁ የታገዱበት ኢሕአፓ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰብዓዊ መበት መከበር ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በወያኔ አገዛዝ እየተደረጉ ያሉትን  የመብት ጥሰቶች አስመልክቶ ተቃውሟቸውን እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ እየጠየቀ የሚገኘው። የወያኔን አገዛዝ በተለያየ ደረጃ የሚደግፉ እንደ እንግሊዝ፣ አሜሪካና ሌሎችም ባዕዳኖች ሁሉ እንዲሁ እያደረጋቸው ያሉትን ሳንሱርና የዜና እገዳዎች እንዲያቆም ተቃውሟቸውን እንዲያቀርቡ አሁንም አበክሮ ይጠይቃል።

አፕሪል 17 ቀን 2014 ዓ.ም.

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email** ESPIC@aol.com
**Website** WWW.EPRP.com

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**